የጦጣ ፈንጣጣ

ምን ማወቅ እንደሚገባ፣ ምን ማድረግ እንደሚገባ

የጦጣ ፈንጣጣ ብርቅዬ የሆነ ነገር ግን ከባድ የቫይረስ በሽታ ሲሆን በመደበኛነት በማይከሰትበት እንደ አሜሪካ ያሉ ሃገራት ላይ የተከሰተ ወረርሽኝ ነው። ከኮቪድ-19 በተለየ ይህ አዲስ ነገር አይደለም ነገር ግን ስለስርጭቱ የጤና ባለሙያዎች አሁንም ድረስ በተጨማሪ እየተማሩ ነው።

በአደጋ ውስጥ ያለው ማን ነው

የጾታ ማንነቱ ወይም የወሲብ ዝንባሌው ምንም ይሁን ምን ማንኛዉም ሰው የጦጣ ፈንጣጣ ሊይዘው ይችላል። ሁሉም ባይሆኑም በርካቶቹ ኬዞች ወንዶች ሆነው ከወንዶች ጋር ወሲብ እንደሚፈጽሙ እራሳቸውን የለዩ (MSM) የሰዎች ማህበረሰብ ማካከል የሚገኙ ናቸው።

ዝግጁ ይሁኑ፤

- ምልክቶች ካሉ ይከታተሉ
- እንዴት እንደሚሰራጭ ይወቁ
- የመከላከል እርምጃዎችን ይውሰዱ
- ካስፈለገ ለዶክተርዎ ይደውሉ

ምልክቶች ካሉ ይከታተሉ



በጣም የተለመደው ምልክትበፊት ላይ፣ በአፍ ውስጥ እና በእጆች፣ በእግሮች በደረት፣ በመራቢያ አካላት ወይም በፊንጢጣ የመሳሰሉ ሌሎች የሰውነት አካላት ላይ እና ውስጥ በመሆን እንደ ብጉር ወይም አረፋ የሚመስሉ ሽፍታ ወይም ቁስሎች (የጦጣ ፈንጣጣ የ‘ፈንጣጣው’ አካል) ነው።

አንዳንድ ሰዎች በመጀመሪያ የሚከተሉት ምልክቶች ሊኖሩባቸው ይችላል፣ ወይም ከሽፍታ ወይም ቁስሎች በተጨማሪ፦

- ትኩሳት
- ያበጡ ንፍፊቶች
- የራስ ምታት
- ድካም
- የጡንቻ ህመም/የጀርባ ህመም
- ብርድ ብርድ ማለት

ምልክቶች አብዛኛውን ጊዜ ከመጋለጥ በኋላ ከ7-14 ቀናት በኋላ ሊታይ ይችላል ነገር ግን ከ 5-21 ቀናት ሊቆይ ይችላል። ህመሙ በተለምዶ ከ2-4 ሳምንታት ይቆያል።

እንዴት እንደሚሰራጭ ይወቁ

የጦጣ ፈንጣጣ በተለምዶ የሚሰራጭበት መንገድ ከቆዳ፣ ከልብሶችም ከአልጋ ልብስ ወይም በቫይረሱ ከተያዘ አንድ ሰው ሰውነት ውስጥ ከወጣ ፈሳሽ ነው። ሰዎች ምልክቶች ከጀመሩበት ሁሉም ቁስሎች እስከሚድኑበት እና አዲስ የቆዳ ንብርብር እስከሚፈጠርበት ድረስ አስተላላፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

የጦጣ ፈንጣጣ ያለበት አንድ ሰው ለምሳሌ ፊትዎ ቀርቦ ቢያስል ወይም ቢያስነጥስ በትላልቅ የመተንፈሻ ጠብታዎች በኩል እንዲሁ ሊሰራጭ ይችላል።

ኢንፌክሽኑን ይከላከሉ

- በቅርብ ስለነበረ ህመም እና በተለይ ደግሞ ማንኛዉም አዲስ ወይም ምክንያታቸው የማይታወቅ ቁስሎች ወይም ሽፍታዎች የመራቢያ አካልዎ እና ፊንጢጣዎን ጨምሮ በሰውነትዎ ላይ ሲወጣ ከወሲብ አጋር(አጋሮችዎ) ጋር ይነጋገሩ።
- ማንኛዉም ሰው አዲስ ወይም ያልተጠበቀ ሽፍታ ወይም ቁስል ካለበት፣ ወሲብ አይፈጽሙ ወይም የቅርብ አካላዊ ንክኪ አያድርጉ።
- ከእያንዳንዱ ወሲብ ወይም ሌላ የቅርብ ንክኪዎች በፊት እና በኋላ እጆችዎን፣ የወሲብ መጫወቻዎች እና የአልጋ ልብስን ይጠቡ።

ወደ ክለቦች፣ የጭፈራ ቦታዎች፣ ሳውናዎች፣ የወሲብ ፓርቲዎች እና የቆዳ ለቆዳ ወይም የፊት ለፊት ግንኙነት ያለባቸው በርካታ ሰዎች ያሉባቸው ሌሎች ቦታዎች መሄድ፣ የጦጣ ፈንጣጣ ተጋላጭነት አደጋን ይጨምራል።

ያለን የክትባት አቅርቦት የተወሰነ ነው፡፡ ድህረገፁን redcap.link/AHD-MPV በመጫን መስፈርቱን እንደሚያሟሉ ካረጋገጡ በሓላ ተመዝግበው ይጠባበቁ

ዶክርተዎ ጋር ይደውሉ

ለጦጣ ፈንጣጣ ሊጋለጡ ወይም ምልክቶች ሊኖርብዎ እንደሚችል ያስባሉ? መመርመር እንዳለብዎ ለማወቅ ዶክተርዎን ያነጋግሩ። የአሌክሳንድሪያ የጤና መምሪያ እርስዎን በቀጣይ እርምጃዎች ለመምራት ከአካባቢ ጤና አገልግሎት ተቋማት ጋር እየሰራ ይገኛል። እርስዎን በጤና በጤና ተቋማቱ ግምገማ ማድረግ እስኪቻል ድረስ ከሌሎች ጋር ያለዎትን የቀጥታ ንክኪ ያስወግዱ።

የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ኢንሹራንስ የለዎትም? አሌክሳንድሪያ የጤና መምሪያን በ 703.746.4988 ይደውሉ

የበለጠ ለማወቅ ወደ **ALEXANDRIAVA.GOV/MONKEYPOX** ይሂዱ